# የሰርቫይቨር ሊደርሺፕ ማመልከቻ መመርያ

የዚህ ፈንድ አላማ ከዘመናዊ ባርነት በህይወት የተረፉ እና የብዝበዛ ለምሳሌ፡ የህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር፣ የአስገዳጅ የጉልበት ስራ፣ የአስገዳጅ የሰዎች ጉልበት ብዝበዛ ስራ፣ የአስገዳጅ ጋብቻ የህይወት ተሞክሮ ባላቸው ሰዎች የሚመሩ ድርጅቶችን መደገፍ ነው። በኢትዮጵያ፣ በኡጋንዳ ወይም በታንዛኒያ የሚገኙ ከዘመናዊ ባርነት በህይወት በተረፉ ሰዎች የሚመሩ ድርጅቶች ለማመልከት እንኳን በደህና መጣችሁ። ተጨማሪ ድጋፍ ከፈለጉ ወይም ይህን ማመልከቻ ለመሙላት ከተቸገሩ እና ድጋፍ ካስፈለግዎት፣ እባክዎን በዚህ ኢሜይል **SLF@freedomfund.org** ያገኙን።

1. **የድርጅትዎ ስም ማን ይባላል?**

   እባክዎ የድርጅትዎን ህጋዊ ስም ያስገቡ። ድርጅትዎ የተመዘገበ ከሆነ፣ እባክዎ በተመዘገበበት ሀገርብ ውስጥ የተመዘገበበትን ስም ያስገቡ።

2. **ድርጅትዎ የት ነው የሚገኘው?**

   እባክዎ ድርጅትዎ የሚገኚበትን አድራሻ ያስገቡ።

   ሀገር፡

   ክልል፡

   ክፍለ ከተማ፡

   ወረዳ/ቀበሌ:

3. **እርስዎ የሚገኙበት አድራሻ ምንድን ነው?**

   ይህንን ማመልከቻ የሚሞላ ሰው ስም እና አድራሻ ያስገቡ።

   ስም:

   የኢሜል፡-

   ስልክ ቁጥር፡-

   የድርጅትዎ የፖስታ አድራሻ፡-

4. **እርስዎን ለማግኘት የተሻለ መንገድ የቱ ነው? (እባክዎ አንዱን ያክብቡ)**

ከታች ከተዘረዘሩት ሁለት አማራጮች መካከል እባክዎን ከድርጅትዎ ጋር ለመገናኘት የተሻለው መንገድ የቱ ነው (በስልክ ጥሪ ወይም በኢሜል)? እባክዎ አንድ ብቻ ይምረጡ።

በስ ልክ፡

ኢሜይል፡

5. **ከእኛ ጋር የተሻለ ግንኙነት ወይንም ተግባቦትን ሊፈጥርሎት የሚችለው ቋንቋ የቱነው?**

እባክዎ በስልክ ጥሪ ወይም በኢሜል ከእኛ ጋር የተሻለ ተግባቦትን ሊፈጥርሎት የሚችለውን ቋንቋ ይግለጹ። ከእንግሊዘኛ ቋንቋ ውጪ ከሆነ እንደአስፈላጊነቱ ለትርጉም እና ለትርጓሜ እናመቻቻለን።

6. **የድርጅትዎ ራዕይ፣ ተልዕኮ ወይም ትኩረት ምንድን ነው? (ቢበዛ በ200 ቃላት ብቻ ይግለጹ)**

እባክዎ የድርጅትዎን ተልእኮ እና አጠቃላይ ግቦችን ይዘርዝሩ፤ እንዲሁም ማሳካት የሚፈልጉትን አላማ ይጥቀሱ።

**ለምሳሌ**፣ የፍሪደም ፈንድ **ተልእኮ** እውቀትን፣ ሀብትን እና ፍቃደኝነትን በማስተባብ ባርባርነትን ማስቆም ነው። የፍሪደም ፈንድ **ራዕይ** ከባርነት የጸዳች ዓለም ማየት ነው። የፍሪደም ፈንድ **ትኩረት** ዘመናዊ ባርነት በተስፋፋባቸው ሀገራት እና ዘርፎች ላይ እጅግበጣም ውጤታማ የግንባር ቀደም የሆኑ ጥረቶችን በመለየት ኢንቨስት ማድረግ ነው።

7. **የድርጅትዎ አይነት እና መዋቅር ምንድነው? (ቢበዛ በ100 ቃላት ብቻ ይግለጹ)**

እባክዎን የድርጅቱን **አይነት** ይግለጹ - ለምሳሌ የበጎ አድራጎት ድርጅት፣ የሰራተኛ ማህበር፣ ህብረት ማህበር፣ ማህበራዊ ድርጅት ወይም ኔትወርክ ነው?

እባክዎ የድርጅትዎን **መዋቅር** ይግለጹ - ለምሳሌ ቦርድ፣ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ወይም የአስተዳደር ቡድን አለዎት?

**8. በድርጅትዎ ውስጥ ምን ያህል ሰራተኞች አሉ?**

እባክዎ የድርጅትዎን ቋሚ ሰራተኞችን፣ የኮንትራት ሰራተኞችን እና በጎፈቃደኞችን ጨምሮ በአጠቃላይ የሰራተኞችን ብዛት ይግለጹ።

**9. በአሁኑ ሰዓት የድርጅትዎ ፕሮግራሞች ወይም ተግባራት ምን ምን ናቸው? (ቢበዛ በ200 ብቻ ይግለጹ)**

እባክዎን በጥቂት ዓረፍተ-ነገሮች አሁን ያሉትን ፕሮግራሞችን፣ ተግባራትን ወይም ፕሮጀክቶችን (ለምሳሌ፡ የግንዛቤማስጨበጫፕሮግራሞችን፣ ከባርነት እና ከህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር በሕይወት የተረፉትን ድጋፍ መስጠት፣ መሟገት - ድምጽየመሆን)።

**10. እርስዎ ወይም ሌላ የድርጅትዎ አባል ሰራተኛ ከዘመናዊ ባርነት በሕይወት የተረፈ ሰው ወይም የብዝበዛ የሕይወት ተሞክሮ ያለው ሰው ለይተው ይታወቃሉ? (እባክዎ አንድን ብቻ ያክብቡ)**

እርስዎ ወይም በድርጅትዎ ውስጥ ያሉ ሌሎች ሰራተኞች እንደ ከዘመናዊ ባርነት በሕይወት የተረፈ ሰው ወይም የብዝበዛ የሕይወት ተሞክሮ ያለው ሰው ካለ እና ተለይተው የሚታወቁ ከሆኑ እባክዎን 'አዎ' የሚለውን ይምረጡ። ከዘመናዊ ባርነት በሕይወት የተረፈ ወይም የብዝበዛ የህይወት ልምድ ያለው ሰው በአስገዳጅ የጉልበት ሥራ፣ በሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር፣ የአስገዳጅ የሰዎች ጉልበት ብዝበዛ፣ ወይም አስገዳጅ ጋብቻ ተጋልጠው የነበረ ሰው ነው።

በድርጅትዎ ውስጥ ከዘመናዊ ባርነትና ብዝበዛዎች በሕይወት የተረፉ እና የሚታወቁ ከሌሉ እባኮትን 'አይ' የሚለውን ይምረጡ።

እርግጠኛ ካልሆኑ ወይም ይበልጥ በዝርዝር ለማብራራት ከፈለጉ፣ እባክዎን 'ሌላ' የሚለውን ይምረጡ እና የድርጅትዎን ሁኔታ የሚገልጹ አንድ ወይም ሁለት ዓረፍተ-ነገሮችን ይጻፉ።

አዎ

አይ

ሌላ (እባክዎ ያብራሩ)፡

**11.በድርጅትዎ ውስጥ ከዘመናዊ ባርነት በሕይወት በተረፉ ሰዎች የተያዘ የስራ ኃላፊነት ወይም ማዕረግ ምንድናቸው?**

ድርጅትዎ ከዘመናዊ ባርነትና ብዝበዛዎች በሕይወት የተረፈ ወይም የብዝበዛ የሕይወት ተሞክሮ ያላው ሰራተኛ እና/ወይም አመራር ካለው እባክዎን በድርጅትዎ ውስጥ የያዙትን የስራ ኃላፊነት በታዎችን ወይንም የሙያ ማዕረጎችን ብቻ ይዘርዝሩ (ለምሳሌ፡ ዳይሬክተር፣ ሥራ አስኪያጅ)። በእነርሱ የተያዘውን የስራ ኃላፊነት እና ማዕተጎችን እንጂ ስማቸውን መዘርዘር አስፈላጊ አይደለም።

**12. ድርጅትዎ ሴፍጋርዲንግ (የደህንንነት) ፖሊሲ አለው**?

ሴፍጋርዲንግ (የደህንነት) ፖሊሲ ወይም የሴፍጋርዲንግ ተግባራትን ሚያከናውኑ የመከላከያ ፖሊሲዎች ካልዎት ከታች ካሉት አማራጮች እባክዎ "አዎ" የሚለውን ይምረጥ።

እባክዎ ከላይ ከተገለጹት አማራጮች ውስጥ አንዳቸውም ከለሎዎት “አይ” የሚለውን ይምረጡ።

እርግጠኛ ካልሆኑ ወይም ይበልጥ በዝርዝር ለማብራራት ከፈለጉ፣ እባክዎን 'ሌላ' የሚለውን ይምረጡ እና የድርጅትዎን ሁኔታ የሚገልጹ አንድ ወይም ሁለት ዓረፍተ-ነገሮችን ይጻፉ።

አዎ

አይ

ሌላ (እባክዎ ያብራሩ)

**13.ሁሉም የድርጅትዎ ሰራተኞች እና የማህበረሰብ አባላት ደህንነታቸው የተጠበቀ እና የተከበሩ መሆኑን የማረጋግጡበት መለክያዎች አልዎት? (እባክዎ አንዱን ይምረጡ)።**

ድርጅትዎ ሰራተኞቹን እና የፕሮግራሙን ፣ የፕሮጀክቱን እና የተግባራቱን ተቀባዮች ሁሉ ከጥቃት እና ብዝበዛ የተጠበቁ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ፖሊሲ ወይም ፕሮቶኮል አለው?

ፖሊሲ ወይም ፕሮቶኮል ካለዎት ''አዎ'' ብለው ይምረጡ። ከሌለው ''አይ'' የሚለውን ይምረጡ።

ፖሊሲው በአሁኑ ጊዜ እየተዘጋጀ ከሆነ፣ ወይም እርግጠኛ ካልሆኑ ወይም ሁኔታውን ይበልጥ በዝርዝር ለማስረዳት ከፈለጉ ''ሌላ'' ይምረጡ።

አዎ

አይ

ሌላ (እባክዎ ያብራሩ)

**14. ድርጅትዎ በአገርዎ ውስጥ ተመዝግቧል? (እባክዎ አንዱን ይምረጡ)**

ድርጅትዎ በአገርዎ ህጋዊ ተቋም ሆኖ ከተመዘገበ ''አዎ'' የሚለውን ይምረጡ። ድርጅትዎ በአገርዎ ካልተመዘገበ ''አይ'' የሚለውን ይምረጡ። ድርጅትዎ በአሁኑ ጊዜ በመመዝገብ ሂደት ላይ ከሆነ 'በሂደት ላይ ነው' የሚለውን ይምረጡ።

አዎ

አይ

በሂደት ላይ ነው

**15. ድርጅትዎ የባንክ አካውንት/ሂሳብ አለው? (እባክዎ አንዱን ብቻ ይምረጡ)**

ድርጅትዎ በድርጅቱ ስም የተከፈተ የባንክ አካውንት/ሕሳብ ካለው፣ እባክዎን 'አዎ' የሚለውን ይምረጡ። ድርጅትዎ በራሱ ስም የተከፈተ የባንክ አካውንት/ሂሳብ ከሌለው ወይም የግለሰቦችን/በግለሰቦች የተከፈተ የባንክ አካውንት/ሂሳብ የሚጠቀም ከሆነ፣ እባክዎ 'አይ' የሚለውን ይምረጡ። የእርስዎ ድርጅት በአሁኑ ጊዜ የባንክ አካውንት/ሕሳብ ለመክፈት በሂደት ላይ ከሆነ፣ እባክዎን 'በሂደት ላይ' የሚለውን ይምረጡ።

አዎ

አይ

በሂደት ላይ ነው

**16.አዎ ከሆነ፣ የባንክ አካዉንት/ሕሳብ ፈራሚዎች እነማን ናቸው?**

እባክዎ በድርጅቱ የባንክ ሒሳብ ላይ ፈራሚ ተብለው የተሰየሙትን ሰዎች ስም ይዘርዝሩ ይግለፁ። እነኚህ ሰዎች የድርጅቱን የገንዘብ ፍሰት የሚያንቀሳቅሱ እና የሚቆጣጠሩ እንዲሁም የድርጅቱን ሂሳብ የሚከታተሉ ሰዎች ናቸው።

**17. ድርጅትዎን ለመደገፍ ይህንን ፈንድ እንዴት ይጠቀሙታል? (ቢበዛ 200 ቃላቶችን በመጠቀም ያብራሩ)**

ይህ ፈንድ ብሰጠዎት፣ ገንዘቡን እንዴት ጥቅም ላይ ይውላል ብለው ያስባሉ? **ምሳሌ፡-** ለሰራተኞች ኮምፒውተሮችን መግዛት፣ የቢሮ ኪራይ፣ ሰራተኞችን መቅጠር፣ ፕሮግራም መደገፍ፣ ወዘተ። አጭር ማብራርያ በቂ ነው፤ ምክንያቱም ገንዘቡን እንዴት ማውጣት እንደሚችሉ ለማየት እና የገንዘብ ድጋፉን ካገኙ አስገዳጅ አለመሆኑን ለማሳየት ነው።

**18. ድርጅትዎ ከላይ የተዘረዘሩትን ፕሮግራሞች እና ተግባራቶችን ለመከወን የገንዘብ ምንጮች አለው?**

ድርጅትዎ የገንዘብ ምንጮች ካለው፣ እባክዎ ከታች ከተዘረዘሩት አማራጮች “አዎ” ብለው ይምረጡ። ድርጅትዎ የገንዘብ ምንጮች ከሌለው፣ “አይ” ብለው ይምረጡ። ማብራራት ከፈለጉ “ሌላ” የሚለውን ይምረጡ።

አዎ

አይ

ሌላ

**19. ድርጅትዎ በአሁኑ ጊዜ የፍሪደም ፈንድ አጋር ወይም ፈንድ ተጠቃሚ ነውን?**

በአሁኑ ጊዜ ፈንዶችን እያገኙ ነው ወይስ ከፍሪደም ፈንድ ጋር በአጋርነት ፕሮግራሞችን በመስራት ላይ ይገኛሉ? አዎከሆነ፣ እባክዎን ከፍሪደም ፈንድ ጋር ያለዎትን አጋርነት በዝርዝር ይግለፁ።

አዎ

አይ

አዎ ከሆነ፣ እባክዎን አጠር በማድረግ ይግለጹ፡-

**20.ስለ ዚህየገንዘብድጋፍእድልእንዴትሰሙ?**

እባክዎ ስለ ሰርቫይቨር ሊደርሺፕ ፈንድ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደት እንደሰሙ እና ለማወቅ እንደቻሉ ይግለጹ። ለምሳሌ፣ ፌስቡክ ወይም ትዊተር ወይም በባልደረባ ወይም በጓደኛ በኩል ሊሆን ይችላል።

**21.እባክዎ የድርጅትዎን ድህረ-ገፅ እና የማህበራዊ ሚዲያ ሊንኮችን ይዘርዝሩ።**

እባክዎን ወደ ድርጅትዎ ድህረ-ገፅ እና ሁሉም የድርጅትዎትን ማህበራዊ ሚዲያ ገጾች የሚያመሩ ሊንኮችን ያጋሩን።

**22. እባክዎን ድርጅትዎን እና ስራዎን የሚያውቁ የሁለት ሰዎች ስም ይጥቀሱ።**

እባክዎን ስለ ድርጅትዎ እና የድርጅትዎን ስራ የሚያውቁ የሁለት ሰዎች ስም እና አድራሻ ይፃፉ።

እነሱም አጋር ድርጅት፣ የማህበረሰብ አባል፣ የፕሮግራም ተጠቃሚ ወይም ሌላ በማንኛውም የስራ ዘርፍ አብረው የሰሩ ሊሆኑ ይችላሉ። ስለ ድርጅትዎ ለማወቅ እና ለማረጋገጥ እነዚህን ሁለት ሰዎችን ልናናግር እንችላለን።

የአንደኛ ሰው ስም፡

የአንደኛ ሰው ኢሜል፡-

የሁለተኛ ሰው ስም፡

የሁለተኛ ሰው ኢሜል፡-